# አብዮታዊት ኢትዮጵያ 19



ሌ/ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው፣



ዶክተር ሰናይ ልኬ ።

“ለውጊያ ዘመቻ–
የምታቀርበው ሀሳብ
የምታዘጋጀው ዕቅድ
የምታሳልፈው ውሳኔ
የምትሰጠው ትዕዛዝ–
በተዋጊው
ሠራዊት
ደም
የሚጻፍ ነው።

ዳንኤል አስፋው

ጥር ፴ ፲፱፸፱ዓ.ም.

ርእሰ አንቀጽ

# አብዮታዊ መኰንንና አብዮታዊ ምሑር

ጥር ፳፮ ቀን ፲፱፻፸፬ ዓ.ም. የጥቂት የውስጥ አርበኞችን ሴራ ለማክሸፍ በተደረገው ትንንቅ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ገና ለረዥም ጊዜ መተኪያ የማያገኙላቸው አንድ አብዮታዊ መኰንንና አንድ አብዮታዊ ምሑር ወድቀውባቸዋል ።

በየካቲት ፲፱፻፷፮ ዓ. ም. ፈንድቶ ያለማቋረጥ እየተቀጣጠለ የመጣው የአብዮታችን ታሪክ ለመጭው ትውልድ በሚተላለፍበት ወቅት በዚህ በተወሳሰበ ትግል ውስጥ ገና ከመጀመሪያው አንስቶ እስከ ዕለተ ሞታቸው ድረስ እነዚህ ሁለት የኢትዮጵያ ልጆች በዚህ በአብዮትና በድል ታሪክ ውስጥ በደማቸው የከፈሉት የክብር ገጽ እንደሚያዝላቸው የነዚህን ሁለት ጓዶች ትግል ጠጋ ብሎ ለማየት የታደለ የትግል ጓድ ሁሉ የማይጠራጠረው ሐቅ ነው ።

አብዮታዊው ኰሎኔል ዳንኤል አስፋው በዚህ አብዮታዊ ትንንቅ ውስጥ ፀረ አብዮት ኃይሎችን እየተቋቋመ ፤ የአብዮቱን ድሎች ላለማስነካት ሌት ተቀን ነቅቶ የመጠበቅ ከባድ ብሔራዊና አብዮታዊ ኃላፊነት የተጣለበት «የአብዮት ጥበቃና ዘመቻ መምሪያ» ኃላፊ ሆኖ የተዋጋ ብርቱና ቆራጥ ታጋይ ነበር ። ዳንኤል አስፋው ሀገራችን ኢትዮጵያ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ካፈራቻቸው ቆራጥ አብዮታውያን ልጆቹዋ ውስጥ አንዱ እንደነበረ ይህንን አብዮት ከአጥፊዎቹ በመከላከል መቅሰፍት ሆኖ የቆየበት የትግል ዘመኑ ለዘለዓለም ይመሰክርለታል ።

ዳንኤል አስፋው በዚህ አብዮታዊ የትግል ወቅት ከአንድ አብዮታዊ መኰንን የሚጠበቁትን ተሰጥኦዎች በሙሉ አስተባብሮ የያዘ መኰንን ነበር ። ዳንኤል አስፋው አብዮቱንና እናት አገሩን አጥብቆ ይወድ ነበር ፤ ሰፊው የኢትዮጵያ ሕዝብ የጣለበት ከባድ ኃላፊነት በዚህ በተወሳሰበ የትግል ወቅት ፋታ የሚሰጠው አልነበረም ። በዚህም ምክንያት ለሚወዳት አብዮታዊት እናት አገሩ ሕልውናና ደኅንነት የቤተሰብ ኑሮውን የረሳ ሌት ተቀን ሥራው ላይ አተኩሮ ሲታገል የወደቀ አብዮታዊ ነበር ።

ዳንኤል አስፋው ደፋርና ቆራጥ ነበር ። ጭንቀቱና ጥበቱ ለዚች እናት አገራችን ከወደቀችበት መነሳትና በሶሻሊዝም ጐዳና ላይ ወደፊት መግፋት ነበር ። ደግሞ ደጋግሞ ሲል ይሰማ እንደነበረው «እኛስ እናልፋለን ይህ አብዮታችን ብቻ ይግፋ» እያለ እንጂ በተሜነበት ከባድ ኃላፊነት ሳያማርር ፤ በዚህ ኃላፊነቱ የተነሳ ሌት ተቀን ተጐዳኝቶት በኖረው የሞት አደጋ ፤ ሲደናገጥና ሲሸበር ያልታየ ፤ አደጋ ባለበት ሁሉ ትእዛዝ በመስጠት ሳይወሰን ከትግል ጓዶቹ ጐን ሆኖ የሚጋፈጥ አብዮታዊ ነበር ።

ዳንኤል አስፋው በእንዲህ ዓይነቱ ፍጥነትን በሚጠይቅ ማወላወልን በማይፈቅድ የሞት ሽረት ትግል ጊዜ ተገቢውና አስፈላጊው ፈጣንነት የተዋሐደው መኰንን ነበር ። ነገር ግን ይህ ቆራጥነቱና ፈጣንነቱ ችኩል አላደረገውም ። በፍጥነት የሚሰጣቸው ውሳኔዎች ሁሉ የታሰበባቸውና ትክክለኛ ውሳኔዎች እንጂ በንዝህላልነት የሚወረወሩ አልነበሩም ።

ይህ ራሱ ዳንኤል አስፋው በዚህ ትግል ውስጥ የመምራት ኃላፊነት ለተሰጠው መለዮ ለባሽ ጓዶቹ ለሰው ልጅ ሕይወት ክቡርነት ፤ ለተጣለበት ኃላፊነት የነበረውን ፍቅርና መጠበብ የሚያሳይ ከአንድ ቆራጥ አብዮታዊ የሚጠበቅ ነበር ።

ከዚህ ለአብዮታዊት እናት አገሩ ባለው ወሰን የሌለው ፍቅር የተነሳ ለፀረ አብዮት ኃይሎች መቅሰፍት ሆኖ ከቆየ መኰንን ጋር ሁለት አብዮታዊ መለዮ ለባሾች ማለትም ሃምሳ አለቃ ዳምጠው ጓንጉልና ፤ ምክትል አሥር አለቃ በላቸው አርጋው አብረው የወደቁ ሲሆን ፤ በዚሁ አብዮቱን ከጥፋት ለመጠበቅ በተደረገው ትግል አንድ አብዮታዊ ምሑር ከመለዮ ለባሽ ጓዶቹ ጐን እንደተሰለፈ ሕይወቱን ለአብዮታዊት እናት አገራችን ሰውቷል ።

አብዮታዊው ምሑር ዶክተር ሠናይ ልኬ በ፴፫ ዓመቱ ከፀረ አብዮተኞች ጋር ሲተናነቅ ገና በለጋነቱ ቢቀጭም በዚች አጭር ሕይወቱ ብዙ ረዥምና አኩሪ የታሪክ ምዕራፎችን ጽፎ ያለፈ ጓድ ነበር ። የተማሪነት ዘመኑን በተለይም በሰሜን አሜሪካ ትምህርቱን ይከታተል በነበረበት ወቅት የኃይለ ሥላሴን ፋሽስታዊ አገዛዝ ይታገሉ ከነበሩት ተማሪዎች ጋር በግንባር ቀደምትነት የተሰለፈ ጓድና በሰሜን አሜሪካ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበርን በፕሬዚዴንትነት ያገለገለ ጓድ ነበር ።

ሠናይ ልኬ የማርክሲዝም ሌኒንዝምን ፍልስፍና ቲዎሪውን አጠናቆ ማወቅ ብቻ ሳይሆን የዕለት ኑሮውም መመሪያ አድርጐ ከሥራ ላይ እያዋለ ሲታገል ለእናት አገሩ ሕይወቱን የሰዋ አብዮታዊ ምሑር ነበር ። በቀብሩ ሥነ ሥርዓት ላይ ከተያዙት መፈክሮች አንዱ እንዳመለከተው ጓድ ሠናይ የኢትዮጵያ ጭቁኖች ወገንና የወዝ አደሮች መምህር ነበር ።

ይህ የትግል ጓዳችን ለኢትዮጵያ አብዮትና ለእናት አገሩ ሕይወቱን የሰዋው በአድኃሪዎች ጥይት የተመታ ዕለት አልነበረም ። ያለበት የትግል ወቅትና በሚሊዮን የሚቆጠሩ ጭቁኖች ሕይወት የሚወሰንበት ትንቅንቅ እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቅ ነበር ። በዚህ ትንቅንቅ የታጋዮች ሕይወት ሳይሆን ዋናው ቁም ነገር የጭቁኖች ነፃ መውጣትና የኢትዮጵያችን ክብር መሆኑንም ይገነዘብ ነበር ። ስለሆነም ደጋግሞ ይል እንደነበረው ትግሉ አፍላ ውስጥ አውቆ ፤ ፈቅዶና ራሱን ሰውቶ ከገባበት ወቅት አንስቶ ሞትን የተቀበለ ደፋርና ታጋይ ዜጋ ነበር ።

ጓድ ሠናይ በሕይወቱ የከፈለውን ለአብዮቱ ያለውን ፍቅር የሚያክል ለበዝባዥ መደቦች ደግሞ ወሰን የሌለው የመደብ ጥላቻ የሚያሳይ አብዮታዊ ነበር ። በዚህም የተነሳ በየጊዜው ፊት ለፊት የሚጋፈጣቸው ጠላቶቹ እጅግ ከፍተኛ የሆነ የመደብ ጥላቻቸውን የሚያሳርፉበት ታጋይ ነበር ።

በተለይ የቀኝ ክንፍ ንውስ ከበርቴ ደንፊዎች ይህ ጓድ ከመጀመሪያ እስከ መጨረሻ በቆራጥነት የታገላቸውና ያጋልጣቸው ስለነበሩ የዚህን ታጋይ ጓድ ጥሩ ስም ለማጉደፍና ለማጥላላት ያልሰነ ዘሩት አሉባልታና ዘለፋ አይገኝም ። ነገር ግን ጓድ ሠናይን ይህ የአድኃሪዎች ጥላቻ አበራታው እንጂ በምንም ዓይነት ከትግሉ ሜዳ ሸሽቶ እንዲወጣ አላደረገውም ።

ጓድ ሠናይ ከሰዎች ጋር በቀላሉ የሚግባባ ፤ ልበሰፊና ቅን ጓድ ነበር ። በ፴፫ ዓመት ዕድሜው የተለየን ጓዳችን ለኢትዮጵያ ሰፊ ሕዝብ ፤ ለኢትዮጵያ ወዝ አደር መደብ ፤ ለዓለም አቀ ፋዊነት የኖረና ለዚሁ ዓላማ ከአድኃርያን ሲተናነቅ የሞተ ቆራጥ አብዮታዊ ነበር ።

ሌ/ ኰሎኔል ዳንኤል አስፋውና ዶክተር ሠናይ ልኬ በአንዲት ቀን ከአንድ የጋራ ጠላት ጋር ሲተናነቁ መሞታቸው ለኛ በትግል ለምንከተላቸው ታጋይ ኢትዮጵያውያን እጅግ ከፍተኛ ትምህርት ሰጥተውን አልፈዋል ። ከነዚህ ሁለት ጓዶች የምንቀስመው ትምህርት በትግል ሕይወ ታቸው ያሳዩን አርአያነት ብቻ አይደለም ። አንድ አብዮታዊ መኰንንና አንድ አብዮታዊ ምሁር የትግል ሕይወታቸውን ባስተሳሰረው የአብዮታዊት እናት አገር ፍቅር ጐን ለጐን ሲዋጉ መለዮ የማይለየውን አብዮታዊት እየመሰከሩ በጋራ ጠላት ፊት በአንድ ላይ ወድቀዋል ።

ዳንኤልና ሠናይ በትግልና በሞት የተጐዳኙበት ታሪክ መለዮ ለባሹ አብዮታዊና ታጋዩ ምሑር ተዋህደው የኢትዮጵያ አብዮታዊ ልጆች በደማቸው የሚጽፉት የትግልና የድል ታሪክ ነው። አብዮታዊ መለዮ ለባሾችና ምሁራን ከነዚህ ጓዶች ሕይወትና እጅግ ምሳሌነት ካለው ቆራጥ ሞታ ቸው አስፈላጊውን ትምህርት ቀስመን ሁለቱም በጋራ ጠላታቸው ፊት በአንድነት የወደቁበትን አርማ ይዘን ወደፊት እንጓዛለን ። ከእጃቸው የወደቀውን የነፃነት ባንዲራ ከብረት በጠነከረ የአ ብዮታውያን አንድነት አንስተን በነዚህ በማይተኩ ጓዶች የደረሰብንን ትልቅ ኀዘን ወደ ጥንካሬ ለውጠን እስከመጨረሻው ድረስ ለመታገልና ለመሞት ቃል እንገባላቸዋለን ።

በነዚህ ጓዶቻችን ሞት ቁጣው የተቀሰቀሰው ወዝ አደር ከያዛቸው መፈክሮች አንዱ እንደ ሚከተለው ይል ነበር ።

«ዳንኤልና ሠናይ ! በእናንተ ሞት አብዮቱ ተቀጣጥሏል» «በአድኃርያን መቃብር ላይ አዲ ሲቱን ኢትዮጵያን መሥርተን ደማችሁን እንበቀላለን» እኛም ከጭቁኑ የኢትዮጵያ ሕዝብ የተለየ ቋንቋ አንናገርም ። ጓዶችን ለወደቁለት ዓላማ እየታገልንና እየወደቅን በአሳዩን የክብርና የትግል ጐዳና እንገፋለን ። አዲሲቱን ኢትዮጵያን በዳንኤልና በሠናይ ጠላቶች መቃብር ላይ እን መሠርታለን ።

አብዮታዊት እናት አገር !
ወይም ሞት !
ድል የሰፊው ሕዝብ ነው !